መነኩሴውም «ምንም!» በማለት ይመልሳል።

አባ ዮሐንስ ቀጠል አድርጎ «በዮሐንስም ቢሆን እንዲሁ ነው። አየህ ሴቲስ ውስጥ ያሉ መነኮሳት በሙሉ እኔን ለማየት በየቀኑ ቢመጡ እንኳ ከክርስቶስ ፍቅር ሊነጥሉኝ አይችሉም! ስለዚህ ያለ ማቋረጥ ደጋግመህ ወደ እኔ ልትመጣ ትችላለህና አስቸግረው ይሆናል ብለህ እንዳትጠራጠር!» አለው።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የእነዚህን ሁለት አባቶች ጽናት ስለ ተመለከተ በመነኩሴው ላይ ያደረውን የመርሳት አባዜ ፈጽሞ አራቀለት። አያችሁ! በሴቲስ ያሉ መነኮሳት ሕይወት ይህን ይመስላል። እነርሱ በፈተና ውስጥ የሚኖሩትና ከራሳቸው ጋር የሚጣሉትን ሰዎች መልካም ሥራ ይሠሩ ዘንድ መንፈሳቸውን ያነቃቁላቸው ነበር።

18/ አንድ ቀን አንድ መነኮስ ወደ አባ ዮሐንስ ሐጺር ቀርቦ «መንፈሳዊ ወንድሜ ወደ እኔ አዘውትሮ እየመጣ ሥራ እንድሠራ ይነግረኛል። እኔ ግን በሽተኛና ደካማ ስለ ሆንሁ ሥራ ስሠራ ወዲያው ይደክመኛል። ስለዚህ ትእዛዛትን አፈጽም ዘንድ ማድረግ ያለብኝ ምንድር ነው?» በማለት ይጠይቀዋል።

ዮሐንስ ሐጺርም «የዮፎኒ ልጅ የሆነው ካሌብ ለሊያቡ እንዲህ ብሎት ነበር፡- 'የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ ምድርን እስልል ዘንድ ከቃዴስ በርኔ በላከኝ ጊዜ -እኔ የአርባ ዓመት ሰው ነበርሁ . . . አሁንም እነሆ ለእኔ ዛሬ ሰማንያ አምስት ዓመት ሆነኝ። . . .

እንዲሁ ዛሬ ለመዋጋት ለመውጣትም ለመግባትም ጉልበቴ ያው ነው::'» (ኢያ 14:7-11)::

እንተም እንደ ካሌብ ለመውጣትና ለመግባት ብርታቱ ካለህ ወደ ሥራህ ሂድ:: ይህን ማድረግ ካልቻልህ ግን በአትህ ውስጥ ተቀምጠህ ስለ ኃጢአቶችህ ምርር ብለህ አልቅስ:: በዚህ ጊዜ ወንድሞችህ በዐፀት መሞላትህን ሲመለከቱ ለሥራ እንድትወጣ አያስገድዱህም» ብሎ መልሶለታል::

19/ በአንድ ወቅት ደግሞ አባ ዮሐንስ ሐጺር «ዮሴፍን የሸጠው ማነው?» ብሎ ወንድሞቹ መነኮሳትን ጠየቃቸው::

አንዱ መነኩሴ «ወንድሞቹ ናቸው!» በማለት ይመልስለታል::

አባ ዮሐንስ ግን «የሸጡት ወንድሞቹ አይደሉም! 'እኔ ወንድማቸው ነኝ!' ብሎ በተቃውሞ መናገር እየቻለ ዝም ብሎ ስለ ተሸጠ እንዲሸጥ ያደረገው ትሕትናው ነው! ግብፅ ውስጥ ከፈርዖን ቀጥሎ በሥልጣኑ ሁለተኛው ከፍተኛ ሰው እንዲሆን ከፍ ከፍ ያደረገውም ይኸው ትሕትናው ነው::» ብሎ መልሶላቸዋል::

20/ ከዕለታት አንድ ቀን ደግሞ ዮሐንስ ሐጺር:- «ራስን መውቀስ የመሰለውን ቀላል ሸክም ከላያችን ላይ አውርደን ከጣልን በኋላ አሁን የተሸከምነው ራስን ማጽደቅ የተባለውን ከባድ ሸክም ነው!» በማለት ተናግሯል::

21/ «እግዚአብሔርን መፍራትና ትሕትና ከሁሉም የሚበልጥ መልካም ሥራ ነው።» በማለትም አባ ሐጺር ተናግሯል።

22/ ከዕለታት በአንዱ ቀን አባ ዮሐንስ ሐጺር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተቀምጦ በጎዘን ሲያታስት ከኋላው የተቀመጠውን አባት አላየውም ነበር። በመጨረሻ ሲመለከተው ግን እግሩ ሥር ወድቆ «አባ! ገና የመጀመሪያውን ስላላደረግሁ ይቅር በለኝ!» ብሎታል።

23/ «እኛ አንድ ሰው ስናከብር ሰው ሁሉ ያከብረናል፤ አንድ የሆነው እግዚአብሔርን ስንጠላ ደግሞ ሁሉም ሰው ስለሚጠላን እንጠፋለን!» ብሎም ተናግሯል።

ካህኑ አባ ኢሲዶር (ኢስድሮስ)

(ABBA ISIDORE THE PRIEST)

አባ ኢሲዶር የሴቲስ መነኩሴ ሲሆን ለአባ መቃርስ የመጀመሪያ ወዳጁ ነው። ኢሲዶር ሴቲስ ውስጥ ለአበሩት አራት ሣጥበረ መነኮሳት የበላይ ተጠሪ ሆኖ ያገለገለ አባት ነው።

1/ ስለ ሴቲሱ መነኩሴ ስለ አባ ኢሲዶር፡- «ከእናንተ መካከል ወንድሙ የታመመበት ወይም ቸልተኛ የሆነበት ወይም ደግሞ ግልፍተኝነት አሸንፎት ከአርሱ ዘንድ ሲያስወጣው ከወሰነ ወደ እኔ ይዞት ይምጣ» እያለ ይናገር ነበር። ከዚህ በኋላ በዚህ ጎስቋላ መነኩሴ ቦታ ተገብቶ ስለ እርሱ ረኽሮም መካራ በመቀበል ያድነው ነበር።

2/ አንድ ወንድም አባ ኢሲዶር፡- «ለምንድር ነው ርኩሳን መናፍስት የሚፈሩህ?» ብሎ ሲጠይቀው እንዲህ ብሎ ነበር የመለሰለት፡-

«ምንኩስናን መነኩሴ ከሆንኩባት ቀን እንስቶ ተግባራዊ ስላደረግሁና ቁጣ ወደ ከንፈሬ እንዲደርስ ስላልፈቀድኩለት ነው።»

3/ ይህ አባ ኢሲዶር በአባብ ጋጢአት ለአርባ ዓመት ያህል ቢፈተንም ለምጥትም ሆነ ለቁጣ እጅ አልሰጠም።

4/ «ገና ወጣት ሆኜ በበአቴ ውስጥ ሳለሁ ለጸሎቴ ምንም ዓይነት ገደብ አልነበረኝም። የጸሎትን ጊዜ አስመልክቶ ለእኔ ሌሊቱ እንደ ቀኑ ሰፊውን ሰዓት የያዘ ነበር።» በማለት አባ ኡሲዶር በአንድ ወቅት ተናግሮ ነበር።

5/ አባ ጴሜን ስለ አባ ኡሲዶር እንዲህ በማለት አዘውትሮ ይናገር ነበር፦

«ኡሲዶር በየምሽቱ ሰሌን ይታታ ነበር። ወንድሞቹ ወደ እርሱ ጠጋ ብለው 'ስላረጀህ ጥቂት ጋደም በል!' ሲሉት እንዲህ አያለ ይመልስላቸው ነበር፦ «አይሲዶር ሥጋው ተቃጥሎ አመዱ በነፋስ ይበተናል ቢባልም እንኳ እኔነቴን ዘና ላደርግ አልፈቅድም። የእግዚአብሔር ልጅ ወደ ምድር የመጣው ለእኛ ሕይወት መዳን ነውና።»

6/ ይኸው አባ ጴሜን ከዚህ በተጨማሪ ስለ አባ ኡሲዶር ሌላም ነገር ተናግሯል፦

«በአንድ ወቅት ሕሊናው 'አንተ እኮ ታላቅ ሰው ነህ!' ሲለው 'እኔ ከአባ እንጦንስ ጋር ልወዳደር እችላለሁን? እነ አባ ጳሚንን ልመስል እችላለሁን? እንዴትስ እግዚአብሔርን ካስደሰቱት ከሌሎቹ አባቶች ጋር አንድ ልሆን እችላለሁ?' ብሎ ጥያቄውን በጥያቄ መልሶለታል። አባ ኡሲዶር ይህን የሚናገረው በፍጹም ሰላም ውስጥ ሆኖ ነበር።

በሰምች ላይ ክፉ ውጊያ የሚከፍቱት ርኩሳን መናፍስት ከዚህ ሁሉ ድካም በኋላ ወደ ሲያል እንደሚገባ አድርገው በማስፈራራት ሲናገሩት፡- «ወደ ሲያል ብገባም እናንተን ምንጊዜም የማገኛችሁ ከእግሬ በታች ነው!» በማለት ይመልስላቸው ነበር።

7/ አባ ኤሲዶር «ከዕለታት አንድ ቀን ጥቂት የሆኑ ነገሮችን ለመሸጥ ወደ ገበያ ወጥቼ እንዳለሁ ንዴት ሲቀርበኝ ተመለከትሁት። በዚህ ጊዜ ያመጣኋቸውን ነገሮች እዚያው ትቼ ወደ መጣሁበት ተመልሼያለሁ!» እያለ ይናገር ነበር።

8/ ከዕለታት በአንዱ ቀን አባ ኤሲዶር የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳስ ቴዎፍሎስን ለማግኘት ደርሶ ሲመለስ በሴቲስ ያሉ ወንድሞቹ መነኮሳት «በከተማ ውስጥ ምን እየተደረገ ነው?» ብለው ይጠይቁታል።

እርሱም «ወንድሞቼ! እውነቱን ለመናገር ከሊቀ ጳጳሱ ፊት በስተቀር የማንንም ፊት አልተመለከትሁም!» ብሎ ሲመልስላቸው በተናገረው ነገር በጣም ተጨነቁ።

ስለሆነም «አባታችን! በዚያ ችግር ደርሷል ማለት ነው?» ብለው ጠየቁት።

አባ ኤሲዶር መልሶ «አልደረሰም! ይሁን እንጂ ሌሎችን የመመልከት አሳብ እኔን የተሻለ አያደርገኝም!» በማለት

በእነዚህ በተናገራቸው ቃላት መነኰሳት ወንድሞቹ እጅግ ተደነቁ። ከዚህ በኋላ ዐይኖቻቸውን ጥፋት ከመመልከት እንዲከለክሉ ይህ አባባል ይበልጥ ሊያበረታቸው ችሏል።

ታላቁ አባ መቃርስ

(ABBA MACARIUS THE GREAT)

ግብፃዊው ታላቅ አባት አባ መቃርስ የተወለደው በ330 ዓ.ም. ሲሆን የቀደመ ሥራውም ግመል እየነዳ ንጥር (Nitre) የተባለች ቦታ ላይ ንግድ መነገድ ነበር:: እርሱ ሴቲስ ውስጥ ከነበሩት ታላላቅ መነኮሳት ውስጥ ግንባር ቀደሙ ነው:: ምንኩስናን ከተቀበለ በኋላ አንዲት ልጃገረድ በሐሰት «ያስረገዘኝ እርሱ ነው!» ብላ እስክትከሰው ድረስ ይኖር የነበረው በአንዲት አነስተኛ መንደር ውስጥ ነበር:: ከዚህ የሐሰት ክስ ነፃ ከወጣ በኋላ ሴቲስ ገባ:: ከዚህ በታች የተጠቀሱ ታሪኮቹ እንደሚያሳዩን አባ መቃርስ እንደ ሌሎቹ መነኮሳት ከቦታ ወደ ቦታ ይዘዋወር ነበር እንጂ በአንድ ቦታ ላይ ተወስኖ አልተቀመጠም:: ካዚያን (Cassian) ስለ እርሱ ሲናገር «በሴቲስ በረሃ የመኖር መንገድን የጠረገው መቃርስ ነው» ብሏል:: መቃርስን ሁለት ጊዜ ብቻ የጎበኘው ታላቁ አባ እንጦንስ በሕይወቱ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሮበታል::

1/ አባ መቃርስ ስለ ራሱ ሲናገር:- «ገና ወጣት እያለሁ ግብፅ ውስጥ በአንድ በአት ውስጥ ስኖር በመንደሪቱ ውስጥ የጽሕፈት ሥራ እንድሠራ ወሰዱኝ:: እንዲህ ያለው ክብር ለእኔ የሚገባኝ ሰው ስላልሆንሁ ወደ ሌላ ቦታ ሸሽቼ ተቀመጥሁ::

በዚያም አንድ ለእግዚአብሔር ያደረ መልካም ሰው ስላገኘሁ የእጅ ሥራዎቼን ወደ ገበያ እየወሰደ በመሸጥ በሚገባ ያገለግለኝ ጀመር።

ከጥቂት ጊዜ በኋላ በዚያች መንደር ውስጥ የምትኖር አንዲት ልጃገረድ በዲያብሎስ ስለ ተፈተነች የዝሙት ኃጢአት ፈፀመች። ሆዷ እየገፋ መጥቶ እርጉዝ መሆኗ ሲታወቅ ለዚህ ጥፋት ተጠያቂው ማን እንደሆነ በጥያቄ ያፋጥጧታል።

እርሷም «መነኩሴው ነው!» ብላ መልስ ትሰጣለች።

ከዚህ በኋላ ሰዎቹ በቁጥታ ወደ እኔ መጥተው በአንገቴ ላይ በጥላሸት የጠቆሩ ትናንሽ ማሰሮዎችንና ሌሎችም ነገሮችን ካንጠለጠሉ በኋላ ወደ መንደሩ መካከል ወስደው «ይህ መነኩሴ ሴት ልጃችንን አስነውሯል! ስለዚህ ይዛችሁ ውገሩት!» እያሉ በሞትና በሕይወት መካከል ሆኜ እስክወድቅ ድረስ ክፉኛ ደበደቡኝ።

ከዚህ በኋላ አንድ መነኩሴ በዚያ ሲያልፍ ሁኔታውን ስለ ተመለከተ «ይህን እንግዳ መነኩሴ የምትወግሩት እስከ መቼ ድረስ ነው?» በማለት አስጣለኝ።

አስቀድሞ ያገለግለኝ የነበረው ሰው ከኋላዬ ሲከተለኝ እርሱንም «ልታገለግለው የቆምከው መነኩሴ የሠራውን ሥራ ተመለከትህ?» በማለት በስድብ ሙልጭ አድርገው ስላዋረዱት በጎናቸው ተዋጠ።

የልጅቱም ወላጆች «ወደ እርሱ ወስዶ ሊጠብቃት መሐላ ካልገባ በስተቀር እንዳትለቁት!» ብለው አስጠነቀቁ::

በዚህ ጊዜ ከሚያገለግለኝ ሰው ጋር ከተነጋገርሁ በኋላ እርሱ ዋስ ሆኖ አስለቀቀኝ::

ከዚህ በኋላ ወደ በአቴ ሄጄ የሠራኋቸውን ቅርጫቶች በሙሉ ለደበደቡኝ ሰዎች ሰጠኋቸውና «እነዚህን ሽጡና ለባለቤቴ የምትበላውን ነገር ገዝታችሁ ስጧት!» አልኋቸው::

ይህን ብዬ ራሴን «መቃርስ ሆይ! ለአንተ የምትሆን ሚስት አግኝተሃል! ስለዚህ እርሷን የሚያኖር ተጨማሪ ገቢ ስለሚያስፈልግህ ጠንክረህ ልትሠራ ይገባሃል!» አልሁት::

ከዚህ በኋላ ቅርጫቶቼን ቀንና ሌሊት በትጋት እየሠራሁ ሸጬ ወደ እርሷ መላክ ቀጠልሁ:: ከወራት በኋላ ይህቺ ምስኪን ልጅ የመውለጃዋ ቀን ሲደርስ ምጧ ለብዙ ቀናት ቆየባት::

በዚህ ጊዜ ወገኖቿ ተሰብስበው «ምንድር ነው ነገሩ?» ብለው ጠየቋት::

እርስዋም «ምን እንደሆነ አውቃለሁ! በሐሰት የመነከሱውን ስም ስላጠፋሁ ነው! ሊወቀስ የሚገባው እርሱ ሳይሆን እገሌ ነው!» ብላ ያስረገዛትን ሰው ስም ተናገረች::

በዚህ ጊዜ የሚያገለግለኝ ሰው በደስታ እየፈነጠዘ ወደ እኔ መጥቶ «ልጅቱ፡- መነኩሴው ምንም አላጠፋም! እኔ ዋሽቼ ነው!» ብላ እስክትመሰክር ድረስ ፈጽሞ ልትወልድ አልቻለችም ነበር! አሁን በመንደሯ ውስጥ ያሉት ሰዎች ሁሉ ወደ አንተ መጥተው ንስሓ ለመግባት እየተዘገጃጁ ነው።» በማለት ነገረኝ።

ይህን ስሰማ ሰዎች ሊረብሹኝ ይችላሉ ብዬ ስለ ፈራሁ አሁን ወዳለሁባት ወደ ሴቲስ መጣሁ። ወደዚህ ቦታ የመጣሁበት ዋናው ምክንያት ይህ ነው።» ብሏል።

2/ አንድ ቀን ግብፃዊው መቃርስ አባ ጳምቦን ለማግኘት ከሴቲስ ተነሥቶ ወደ ተራራማው ሀገር ወደ ንጥሪያ ሄደ። በዚያ የሚገኙ በዕድሜ የገፉ መነኮሳት አባቶችም «አባታችን! እባክህ ያለህን ቅዱስ ቃል አጋራን!» ይሉታል።

እርሱም፡- «እኔ መነኮሳትን ተመልክቼያለሁ እንጂ ገና መነኩሴ አልሆንሁም! ከዕለታት አንድ ቀን በባእቴ ውስጥ ተቀምጬ ሳለሁ አባቤ ወደ ምድረ በዳ በመውረድ መመልከት የምችለውን ነገር እንድመለከት እየነዘነዘ አሳስቶም አሳስቶምጥ አለኝ። ይህ አሳብ ምናልባት ፈተና ሆኖ ከዲያብሎስ የመጣ ሊሆን ይችላል ብዬ በማሰብ ለአምስት ተከታታይ ዓመታት ከዚህ አሳብ ጋር ስዋጋ ቆየሁ።

ይሁን እንጂ ከዚያ በኋላም ይህ አሳብ ሊተወኝ ስላልቻለ ተነሥቼ ወደ ምድረ በዳ ወረድሁ። ጭልጥ ባለው በረሃ ውስጥ

አንድ ባሕር በመካከለም ደሴት ተመለከትሁ። በምድረ በዳው ውስጥ የሚኖሩ አራዊት ወደዚያ እየመጡ ከባሕሩ ውኃ ይጠጡ ነበር። በአራዊቱ መካከል ሁለት ሰዎች ወደዚያው ሲያመሩ ስመለከት ግን መናፍስት ይሆናሉ ብዬ ስላመንሁ ፈራሁ፤ መላ ሰውነቴም ይንቀጠቀጥ ጀመር።

ሰዎቹ መንቀጥቀጤን ሲመለከቱ «ሰዎች ስለ ሆንን አትፍራ!» አሉኝ።

በመረጋጋት «ከወዴት ነው የመጣችሁት? ወደዚህ በረሃስ እንዴት ልትመጡ ቻላችሁ?» በማለት ጠየቅኋቸው።

እነርሱም «የመጣነው ከገዳም ሲሆን ከአርባ ዓመታት በፊት እዚህ ቦታ ላይ ለመገናኘት ተቀጣጥረን ነበር። አንዳችን ግብፃዊ ስንሆን አንዳችን ደግሞ ሊቢያዊ ነን።» አሉኝና ቀጠል አድርገው «ዓለሙ እንዴት ነው? ውኃው በወቅቱ ይሞላል? ዓለሙ በብልጽግና እየተደሰተ ነው?» በማለት ጠየቁኝ።

እኔም አምንታዬን ገለጽሁላቸውና፦ «መነኩሴ መሆን የምችለው እንዴት ነው?» ብዬ ጥያቄ አቀረብኩላቸው።

ሰዎቹም «በዓለሙ ውስጥ ያለህን በሙሉ ካልተውክ መነኩሴ ልትሆን አትችልም!» ብለው መለሱልኝ።

«እኔ ደካማ ስለ ሆንሁ እንደ አናንተ ይህንን ለማድረግ አልችልም፤» አልኋቸው።

እነዚህ አባቶች ይህን ሲሰሙ «እንደኛ ለመሆን ካልቻልህ ተመልሰህ በአትህ ውስጥ ግባና ስለ ኃጢአትህ አልቅስ፤» አሉኝ።

ትኩር ብዬ አየኋቸውና «ክረምት ሲገባ ሰውነታችሁ በቅዝቃዜ አይደነዝዝም? በበጋ ወራትስ በፀሐይ ሐሩር አይነድም?» በማለት በመገረም ጠየቅኋቸው።

እነርሱ ግን «እንዲህ ባለው ሕይወት ውስጥ እንድንኖር ያደረገው እግዚአብሔር ነው። ስለዚህ በክረምት ሰውነታችን በብርድ አይደነዝዝም፤በበጋም በፀሐይ ሐሩር አይቃጠልም፤» ብለው መልስ ሰጡኝ።

ኧያችሁ መነኮሳት አባቶቼ! አስቀድሜ «እኔ መነኮሳትን ተመልክቼያለሁ እንጂ ገና መነኩሴ አልሆንሁም፤» ያልኋችሁ በዚህ ምክንያት ነው።

3/ አባ መቃርስ በታላቁ በሴቲስ ምድረ በዳ ውስጥ ሲኖር እርሱ የመጀመሪያውና ብቸኛው መነኩሴ ነበር። እርሱ ኮሚናርበት በረሃ ወረድ ብሎ በሚገኘው በረሃ ውስጥ ግን ሌሎች ብዛት ያላቸው ወንድሞች ነበሩ።

ከዕለታት አንድ ቀን አባ መቃርስ የመንገዱን ግራና ቀ
ሲመለከት ሰይጣን በሰው ተመስሎ በሚኖርበት ጎጆ አጠገብ እያለ
ነበር። ሰውየው ከጥጥ ተሠርቶ ዙሪያውን የተበሳሳ ልብስ የለበ
ሲሆን በየቀዳዳው ውስጥ ትናንሽ አገልግሎች አንጠልጥሏል።

በዚህ ጊዜ መቃርስ «ወዴት እየሄድህ ነው?» ብሎ
ጠየቀው።

ሰይጣኑም «የወንድሞችን ሕሊና ልበጠብጥ እየሄድሁ ነው!»
ብሎ መለሰለት።

መቃርስም መልሶ «የእነዚህ ትናንሽ ቅሎች ጥቅም ምንድር
ነው?» ብሎ ይጠይቀዋል።

ሰይጣኑ «ወንድሞች ይቀምሏቸው ዘንድ ምግብ
የያዝኩባቸው አገልግሎች ናቸው!» አለው።

አባ መቃርስም «ይሄ ሁሉ ዓይነት?!» በማለት ጠየቀው።

ዲያብሎስም እንዲህ ብሎ ይመልሳል፡- «አንድ ወንድም
አንዱን ዓይነት ምግብ ሲቀምስ ካልተስማማው ሌላኛውን ዓይነት
ምግብ አቀርብለታለሁ። እርሱም ካልጣመው ሌላውን የምግብ
ዓይነት ይቀምሳል። እንዲህ እንዲህ እያለ የሚስማማውን
እስኪያገኝ ድረስ ከሁሉም ዓይነት ምግብ ይቀምሳል። በመጨረሻ

ግን ከዚህ ሁሉ ዓይነት አንዱን ይመርጣል!» ይለውና በቅጽበት ካጠገቡ ይሰወርበታል።

አባ መቃርስ ሰይጣኑ በሄደበት አቅጣጫ ተመልሶ ሲመጣ እስኪመለከት ድረስ እዚያው ቦታ ላይ ቆሞ ይጠብቀዋል።

ከዚያም አጠገቡ ሲደርስ እያሾፈበት «መልካም ጤና ለአንተ!» አለው።

ሰይጣኑም «እንዴት ጤና ሊኖረኝ ይችላል?» በማለት ይነጫነጭበት ጀመር። መቃሪም ምን ለማለት እንደፈለገ መልሶ ሲጠይቀው፤

«ሁሉም ስለተቃወመኝ አንዳቸው እንኳ በሰላም አልተቀበሉኝም!» ብሎ ይመልስለታል።

አባ መቃርስም «እዚያ ታች ከሚኖሩት ሰዎች መካከል ጓደኛ የሚሆንህ ሰው አጣህ ማለት ነው?» ሲል በድጋሚ ጠየቀው።

ሰይጣኑም፡- «ለነገሩ እዚያ ታች አንድ ጓደኛ ነበረኝ። በእርግጥ እርሱ ቢቀበለኝም ልክ ሲመለከተኝ ያለበትን ቦታ እንደ ነፋስ አቅጣጫውን እየቀያየረ አስቸግሮኛል።» ብሎ መለሰለት።

መቃርስ ይህ ሰው ማን እንደሆነ ሲጠይቀው፡- «ቴዎጴምጠስ! (Theopemtus)» ብሎ ከተናገረ በኋላ ይሰወራል።

ከዚህ በኋላ አባ መርቃስ እርሱ ከሚኖርበት በረሃ በታች ወዳለው ገዳም ይወርዳል። በዚያ ያሉ አባቶች መምጣቱን ሲሰሙ እርጥብ የዘምባባ ዝንጣፊ ይዘው ይቀበሉታል። እያንዳንዳቸው በዚያች ሰዓት ያስቡ የነበረው «ከኮረብታው ላይ ወርዶ የመጣው እኔ ዘንድ ነው!» እያሉ ነበር።

እርሱም አጠገባቸው እንደ ደረሰ ቴምጹምጠስ የሚባለው አባት ማን እንደ ሆነ ይጠይቃቸውና ያለበትን በእት ሲጠቁሙት ወደዚያው ያመራል። ከዚያም ቴምጹምጠስ ገና ሲመለከተው በበአቱ ውስጥ በደስታ ተቀበለው።

በበአቱ ውስጥ ሁለቱ ብቻቸውን ሲቀሩ አባ መቃርስ ቴምጹምጠስን «እየበረታህ ነው?» ብሎ ጠየቀው።

እርሱም «በጸሎትህ ብርታት እየጠነከርሁ ነው! ነገሮች በጥሩ ሁኔታ እየተከናወኑልኝ ነው!» ብሎ መለሰለት።

አረጋዊው መቃርስ መልሶ «አሳቦችህ አይዋጉህም?» በማለት ጠየቀው።

ቴምጹምጠስ አባ መቃርስ የሚለውን ለመቀበል ብቻ በፍርሃት ውስጥ ሆኖ «አሁን ደህና ነኝ።» አለው።

በዚህ ጊዜ አባ መቃርስ «አየህ! እኔ ለእነዚህ ሁሉ ዓመታት በምንኩስና ኖሬያለሁ። ይሁን እንጂ አሁን ድረስ ምን ያህል ሰው

እንደሚያወድሰኝ ተመልከት! ምንም እንኳ መነኩሴ ብሆንም የዝሙት መንፈስ እስካሁን ድረስ ይፈታተነኛል።» ብሎ ነገረው።

ቴዎጴምጠስ ይህን ሲሰማ «እመነኝ አባቴ! እኔንም ይፈታተነኛል!» አለው።

መቃርስም ሌሎች ይዋገኛል ያላቸውን የተለያዩ ፈተናዎችን ተራ በተራ ለቴዎጴምጠስ ሲነግረው እርሱም የሚፈታተኑትን ውጊያዎች አምኖ በመቀበል ያለበትን ሁኔታ በትህትና ነገረው።

በዚህ ጊዜ መቃርስ «እንዴት ነው የምትጸመው?» ብሎ ጠየቀው።

«የምጸመው እስከ ዘጠነኛው ሰዓት ድረስ ነው!»

«የጾምህን ሰዓት ጥቂት አራዝመው! ወንጌልንና ሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍትን በተመስጦ አንብብ! አንድ ባዕድ የሆነ አሳብ በውስጥህ ከተቀሰቀሰ እርሱን ሳይሆን ወደ ላይ ተመልከት፤ በዚህ ጊዜ ሊየሰብ ክርስቶስ ሊረዳህ ወደ አንተ ይመጣል!» በማለት አባ መቃርስ መከረው። አባ መቃርስ ይህን ከመከረው በኋላ በመጣበት አኳኋን ወደ በአቱ ተመልሶ ሄደ።

አባ መቃርስ በዚያ ሆኖ መንገዱን ለሦስተኛ ጊዜ ሲቃኝ ዲያብሎስን ስለ ተመለከተው «አሁን ደግሞ ወዴት እየሄድህ ነው?» ብሎ ጠየቀው።

ዲያብሎስም «የመነኮሳትን የቀደመ ትዝታቸውን ልተሰቅስባቸው እየሄድሁ ነው!» አለው፡፡ ከአጠገቡ ተሰወረ::

ዲያብሎስ በዚያው መንገድ ተመልሶ ሲመጣ ቅዱስ መቃርስ «ወንድሞቼ እንደምን ናቸው?» ብሎ ጠየቀው::

ዲያብሎስ ነገሮች ክፋኛ እንደተበላሹበት ሲነግረው መቃርስ በምን ምክንያት እንደተበላሹ ጠየቀው::

ጠላት ሰይጣንም እንዲህ ሲል ነገረው፡- «ሁሉም ጋግርታም ሆነዋል:: ከሁሉም የባሰበት ደግሞ ቀርቶኝ የነበረውና የሚታዘዘኝ ያ አንድ ወዳጄ ነው:: ምን እንደ ለወጠው አላውቅም!? የሚገርመው አለመታዘዙ ብቻ ሳይሆን ከሁሉም የከፋው ጋግርታም እርሱ ሆኖ መገኘቱ ነው:: ስለዚህ አሁን ከረዥም ጊዜ በኋላ ካልሆነ በስተቀር ዳግም ወደዚያ ቦታ ላልወርድ ወስኜያለሁ!»

ከዚህ በኋላ አባ መቃርስን በቆመበት ቦታ ትቶት እንደ ጉም በኖ ጠፋ:: ቅዱስ መቃርስም ወደ በአቱ ገባ::

4/ ከዕለታት አንድ ቀን ታላቁ ሰው አባ መቃርስ በኮረብታ ላይ ወዳለው ወደ አባ እንጦስ ይሄዳል:: እዚያ ደርሶ የበአቱን መዝጊያ ሲቆረቁር አባ እንጦስ ወጥቶ «ማነህ አንተ?» ብሎ ጠየቀው::

መቃሪም «እኔ መቃርስ ነኝ!» ብሎ ይመልስለታል::

በዚህ ጊዜ አባ እንጦንስ አባ መቃርስን በቆመበት ትቶት ወደ በአቱ በመግባት በሩን በፊቱ ላይ ይዘጋበታል። ከረዥም ቆይታ በኋላ ትዕግሥቱን የተመለከተው አባ እንጦንስ በደስታ ተቀብሎ አስገባውና «ስለ አንተ ከሰማሁ በኋላ ለረዥም ጊዜ ላይህ እናፍቅ ነበር!» አለው።

ከዚያም በእንግዳ አቀባበል ውስጥ ያሉትን ተግባራት አደረገለት። ረዥም መንገድ አቋርጦ ወደ እርሱ ስለ መጣም አረፍ እንዲል ጠየቀው። ምሽቱ ሲደርስ አባ እንጦንስ ጥቂት የዘምባባ ቅጠሎችን ነክሮ ለራሱ እያራሰ ሲያዘጋጅ አባ መቃርስ «እኔም ለራሴ ከቅጠሎቹ እንድነክር ፍቀድልኝ» ብሎ ጠየቀው።

«ትችላለህ!» አለው።

በዚህ መሠረት ብዙ ጥቅል የዘምባባ ቅጠሎችን በውኃ ውስጥ አርሶ አዘጋጀ። ከዚህ በኋላ በጨለማ ውስጥ ተቀምጠው «ስለ ነፍስ ድኅነት» እየተነጋገሩ የእጅ ሥራዎቻቸውን መሥራት ጀመሩ። መቃርስ የሚሠራው የዘምባባ ሰሌን ከርዝመቱ የተነሣ በበአቱ ውስጥ ባለው ዋሻ አፍ ላይ ተንጠለጠለ።

አባ እንጦንስ ንጋት ሲመጣ አባ መቃርስ የሠራውን ሰሌን ርዝመት ተመልክቶ «ከእነዚህ እጆች ውስጥ የሚወጣው ኃይል ታላቅ ነው!» በማለት ተናገረ።

5/ የሉቲስን ጥፋት አስመልክቶ አባ መቃርስ ለወንድሞቹ መነኰሳት ሲናገር እንዲህ ብሎ ነበር፦

«በአት በረግረጋማ ቦታ አጠገብ ከተሠራ የሴቲስ ጥሩት እንደ ቀረበ አወቁ። ዛፎችን ስትመለከቱ ደግሞ ጥሩት በደጃፋችሁ ላይ መሆኑን አስተውሉ። ልጆችን ስትመለከቱ ግን ደበሎ ምቻችሁን እንሥታችሁ ሽሹ!» በማለት ተናግሮ ነበር።

፩/ የመነኰሳት ወንድሞቹን ጽናት የፈለገው አባ መቃርስ አንድ ታሪክ ነግሮአቸዋል። እንዲህ ሲል፦

«ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ሴት ትንሽ ልጇን ይዛ እዚህ ድረስ መጥታ ነበር። ይህ ትንሽ ልጅ በርኩስ መንፈስ የተያዘ ነበር። ስለሆነም እናቱን «ተነሽና ከዚህ ቦታ ወጥተን እንሂድ!» አላት።

እናቱም «ስለ ደከመኝ ከዚህ የበለጠ ልራመድ አልችልም!» ትለዋለች።

በዚህ ጊዜ ያ ትንሽ ልጅ «ተነሽ! እኔ አዝልሻለሁ!» አላት።

ይህን ስለማ የዲያብሎስን ማታለያና ሰዎች ከመልካም ቦታ እንዲሸሹ ለማድረግ ምን ያህል እንደሚተጋ ተመልከቺያለሁ።

፯/ አባ ሲሦይስ (Sisoes) እንዲህ በማለት ተናግሮ ነበር፦

«ከመቃርስ ጋር በሴቲስ ሳለሁ ሰባት ሆነን መኸሮ ለመሰብሰብ ወደ አንድ ማሳ ወጥተን ነበር። በሥራ ላይ እንዳለ

እንዲት ሴት ከበስተኋላችን ስታለቅስ አይመጥኑት። ተይ ብንላትም በደ ልትለን አልቻለችም።

በዚህ ጊዜ አባ መርቃስ የማሳውን ባለቤት ጠርቶ፡- «ይህቺ ሴት ያለማቋረጥ አምርራ እንድታለቅስ ያደረጋት ነገር ምንድር ነው?» በማለት ጠየቀው።

ባለ ርስቱም «ባለቤታ ከአንድ ሰው ላይ በብድር ገንዘብ ከወሰደ በኋላ በድንገት ሞተ። ሚቹ ገንዘቡን የት እንደ ደበቀው አርሷ ልታውቅ ስላልቻለች ባለ ገንዘቡ አርሷና ልጆቿን በባርነት ሊያሳድራቸው ወስኗል።» በማለት መለሰለት።

አባ መቃርስም «የምሳ ሰዓት ፅረፍታችንን ስንወስድ ወደ እኛ እንድትመጣ ንገራት!» አሉው።

ሴቲቱ በተባለው ሰዓት ወደ መቃሪ ስትቀርብ «እንዲህ ያለ ማቋረጥ የምታለቅሺው ለምንድር ነው?» ብሎ ጠየቃት።

እርስዋም፡- «ባለቤቴ ከአንድ ሰው ላይ ገንዘብ በብድር ከወሰደ በኋላ ከመሞቱ በፊት ገንዘቡን የት እንዳስቀመጠው ሳይነግረኝ በሞት ስለ ተለየኝ ነው።» አለችው።

በዚህ ጊዜ አባ መቃርስ «ነይና ባልሽን የት እንደቀበርሽው አሳዪኝ!» ብሏት ወንድሞቹን ይዞ ወደ መቃብሩ ቦታ ሄደ።

ቦታው ላይ ሲደርሱ መቃርስ ሴቲቱን «ወደ ቤትሽ ግቢ» ብሎ አሰናበታት።

ወንድሞቹ መነኮሳት በተመለጠ ሲጸልዩ አባ መቃርስ የሞተውን ሰው «እገሌ እገሌ . . . ገንዘቡን የት ነው የደበቅኸው?» ብሎ ጠየቀው።

አስከሬኑም «የደበቅሁት ቤቴ ውስጥ ካለው የአልጋዬ ግርጌ ሥር ነው!» ብሎ መለሰለት.:

አባ መቃርስም «እስከ ትንሣኤ ዘገባኤ ድረስ በሰላም አንቀላፋ!» አለው።

ይህን የተመለከቱት መነኮሳት ወንድሞቹ በፍርሃት ተሞልተው ስለ ነበር ራሳቸውን ከእግሩ ሥር ጣሉ።

በዚህ ጊዜ ታላቁ አባ መቃርስ:- «እኔ ምንም ስላልሆንሁ ይህ የሆነው ስለ እኔ ሲባል አይደለም። ይልቁኑ እግዚአብሔር ይህንን ተአምር ያደረገው ለመበለቷ ሴትና አባት አልባ ለሆኑት ሕጻናት ልጆቿ ሲል ነው።» ካለ በኋላ «የተጠየቀችውን ትመልስ ዘንድ እግዚአብሔር ከኃጢአት ያነጻት ይህች ነፍስ ምንኛ የታደለች ናት!» አለ።

ከዚህ በኋላ መበለቷን ሴት አስጠርቶ ገንዘቡ የት እንዳለ ነገራት። እርሷም ገንዘቡን አውጥታ ለባለቤቱ በመመለስ ራሷንም

ሆነ ልጆቿን ከባርነት ነፃ አወጣች። ይህን ታሪክ የሰሙ ሁሉ ለእግዚአብሔር ታላቅ ክብር ሰጡ።

፰/ አባ ጴጥሮስ ስለ ቅዱስ መቃርስ እንዲህ በማለት ተናግሯል። «አንድ ቀን አባ መቃርስ ወደ አንድ ወደ ታመመ ባሕታዊ በአት ሄደ። ምንም እንኳ በአቱ ልትወድቅ የደረሰችና ባዶ መሆኗን ቢያውቅም የሚበላ ነገር ይወስድ እንደ ሆነ ይጠይቀዋል።

ባሕታዊውም «ጥቂት የፍራ ፍሬ ጭማቂ ከተገኘ እወስዳለሁ!» አለው።

ብርቱው መቃርስ ይህን ሲሰማ ጥቂት እንኳ አላመነታም! ወዲያውኑ ተነስቶ የታመመው ሰው የጠየቀውን ጭማቂ ለማምጣት እስከ እስክንድርያ ድረስ ሄደ። በጣም የሚደንቀው ግን በወቅቱ ስለዚህ ገዳይ ያወቀ ሰው አልነበረም።

፱/ ከዚህ በተጨማሪ ይኸው አባ ጴጥሮስ ስለ አባ መቃርስ ሲናገር እንዲህ ይል ነበር፦

«አርሱ ሁሉንም መነኮሳት ወንድሞቹን የሚቀበለው በትሕትና ነበር። ከዕለታት አንድ ቀን ጥቂት መነኮሳት ወንድሞቹ ከአነርሱ ጋር ለምን በዚህ ዓይነት መንገድ እንደሚገናኝ ይጠይቁታል።

አርሱም «ለአሥራ ሁለት ዓመታት ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስን ካገለገልሁት በኋላ ይህን ስጦታውን አድሎኛል! አሁን አናንተ ይህን ገዳይ እዚህ ላይ እንዳቆመው ነው የምትጠይቁኝ?»

ብሎ ጥያቄያቸውን መልሰውን በሰጠ ጥያቄ ውስጥ መልሰ ጠይቋቸዋል::

10/ ስለ አባ መቃርስ ብዙዎች የሚናገሩት ነገር አለ:: አባ መቃርስ ወንድሞቹ መነኰሳትን ተዘዋውሮ ሲጠይቅ በራሱ ላይ ያወጣው አንድ የድርጊት መመሪያ ነበረው::

ይህ መመሪያው «ብወንድሞች የወይን ጠጅ ከተጋበዝህ ስለ እነርሱ ፍቅር ስትል ጥቂት ጠጣ! ይሁን እንጂ ስለ ጡጣሃት ስለ እያንዳንዷ መለኪያ ወይን ምንም ውኃ ሳትጠጣ አንድ ቀን አሳልፍ!» የሚል ነበር::

በዚህ መሠረት ወንድሞቹ ዘና ብሎ ልቡን እንዲያሲደስት ወይን ጠጅ ሲያቀርቡለት ራሱን ለመገዳት በደስታ እየተቀበለ ይጠጣ ነበር::

ደቀ መዛሙርቱ ይህን ነገር ሲያውቁ ወደ ወንድሞች መነኰሳት በመሄድ «ስለ እግዚአብሔር ብላችሁ! ካሁን በኋላ ምንም ዓይነት የወይን ጠጅ አትስጡት! በዚህ ከቀጠለ ግን እኛን ለማስደሰት ሲል እርሱ በበአቱ ውስጥ ሊሞት ይችላል!» አሏቸው::

ከዚህ ጊዜ በኋላ ወንድሞቹ መነኰሳት ጥቂቷን የወይን ጠጅ እንኳ ሳያቀርቡለት ተስማሙ::

11/ ከዕለታት አንድ ቀን አባ መቃርስ ከበአቱ በታች ራቅ ብሎ ወደሚገኘው ረግረጋማ ቦታ ከወረደ በኋላ የዘምባባ ቅጠሎችን ቆርጦ በመሸከም ሲመለስ ዲያብሎስ ረዥም እጀታ ያለው ስለታም ማጭድ ይዞ ሲሄድ መንገድ ላይ ያገኘዋል::

በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ ባለው ኃይል ሁሉ ሰንዝሮ ከመታው በኋላ እንዲህ ይለዋል:- «መቃርስ! እኔን በአንተ ፊት አቅመ ቢስ የሚያደርገኝ ይህ ኃይልህ ምንድር ነው? አንተ የምታደርጋቸውን ነገሮች በሙሉ እኔም አደርጋቸዋለሁ! አንተ እንደምትጾም እኔም እጾማለሁ! አንተ ሌሊቱን ሙሉ ንቁ ሆነህ ታድራለህ - እኔም ፈጽሞ አላንቀላፋም! ይሁን እንጂ በአንድ ነገር ትበልጠኛለህ!» ይለዋል::

አባ መቃርስም በምን እንደሚበልጠው ይጠይቀዋል::

ዲያብሎስም «በትሕትናህ ትበልጠኛለህ! በዚህ ምክንያት አንተን መቃወም አልቻልሁም!» አለው::

12/ በሌላ ጊዜ መነኮሳት አባቶች ወደ አባ መቃርስ ቀርበው «ስትበላም ሆነ ስትጾም ሰውነትህ ከሲታ ነው! ይህ የሚሆነው ለምንድር ነው?» ብለው ይጠይቁታል::

አባ መቃርስም እንዲህ በማለት መለሰላቸው:- «የወይን ቅርንጫፎች በአሳት በሚቃጠሉበት ጊዜ እነርሱን ይደግፍ ዘንድ የሚቆመው ቀጭን ቋሚ እንጨት ሙሉ ለሙሉ ነዶ እስኪያልቅ ድረስ እንደ ቆመ ይቆያል:: ልክ እንዲሁ ሰውም ነፍሱን

የሚያነጻው በፈራሃ እግዚአብሔር ነው። በዚህ ጊዜ ፈራሃ እግዚአብሔር ሰውነቱን እንዲህ አድርጎ ያነሳስለታል።»

13/ ከዕለታት አንድ ቀን አባ መቃርስ ከሴቲስ ወደ ቴርኑቲስ (Terenuthis) ይወጣና በዚያ ያድር ዘንድ ወደ አንድ የአሕዛብ ቤተ መቅደስ ይገባል። በዚያ ቤተ መቅደስ ውስጥ ረኽም ዘመን ያስቆጠሩ ጥቂት አሮጌ የራሣ ሳጥኖች ነበሩ። ከሳጥኖቹ መካከል አንደኛውን በመውሰድ እንደ ትራስ ጭንቅላቱን አሳርፎበት ጋደም ይላል።

ይህን ድፍረቱን የተመለከቱት ርኩሳን መናፍስት በቅናት ስለ ተሞሉ ሊያስፈራሩት ልክ አንዲት ሴት እንደሚጣሩ ጮኽ ብለው «እገሊት. . . ወጥተሽ ነይና ገላችንን እንታጠብ!» በማለት መጣራት ይጀምራሉ።

በዚህ ጊዜ ከመቃርስ ሥር እንደ ሞተ መስሎ የሚናገረው ሌላው ርኩስ መንፈስ «አሳዬ ላይ ሌላ አንግዳ ስላለ ልመጣ አልችልም!» አለ።

ይህ ሁሉ ሲሆን አባ መቃርስ አንዳችም አልፈራም! ይልቁኑ በተቃራኒው የራሣ ሳጥኑን ለማረጋገጥ እያንኳኳ «ከቻልህ ተነሥና ወደ ጨለማው ውስጥ ግባ!» በማለት ተናገረ።

ርሱን መናፍስቱ ይህንን ሲሰሙ ባላቸው ኃይል ሁሉ ድካቸውን አውጥተው በመጮኽ «በልጠኸናል! አሸንፈኸናል!» ካሉ በኋላ ግራ በመጋባት ከዚያ አካባቢ ጠፍተው ሄዱ::

14/ ስለ ቅዱስ አባ መቃርስ እንዲህ ተብሎ ተነግሯል:-

«ክፅለታት በአንዱ ቀን ከሴቲስ ብዛት ያላቸው ቅርጫቶችን ሰፍተው ሊሄድ ድካም ስላሸነፈው ሸክሙን አውርዶ አረፍ ካለ በኋላ ጌታዬ ሆይ! ከዚህ በላይ ልንዝ እንደማልችል አንተ በሚገባ ታውቃለህ! ' በማለት ተናገረ:: ከዚህ በኋላ ከመቅጽበት ራሱን ይዞም በርቀት ካለው ዥረት አጠገብ አገኘው::

15/ አንድ አካለ ስንኩል የሆነ ልጅ ያለው አንድ ግብፃዊ ነው ልጁን እንደ ታቀፈ ወደ አባ መቃርስ ደጃፍ ከቀረበ በኋላ እያለቀሰ በዚያ አጋድሞት ራቅ ብሎ ይቆማል::

አባ መቃርስም ጎንበስ ብሎ ልጁን ከተመለከተ በኋላ «ማነው እዚህ ድረስ ያመጣህ?» ብሎ ጠየቀው::

ልጁም «እዚህ ወርውሮኝ የሄደው አባቴ ነው!» አለው::

በዚህ ጊዜ ቅዱስ አባ መቃርስ «አሁን ተነሥና ወደ አባትህ ሂድ!» አለው::

ልጁም በዚያች ቅጽበት ውስጥ ስለ ተፈወሰ ከአባቱ ጋር ከተገናኘ በኋላ ወደ ቤታቸው ሄዱ።

16/ አባ መቃርስ ሌቲስ ውስጥ እያለ አንድ ቀን ከወንድሞቹ ጋር ስብሰባ ተሰብስቦ ካለቃ በኋላ «ወንድሞቼ . . . ሽሹ!» አላቸው።

በዚህ ጊዜ አንዱ መነኩሴ «ስዚህ ምድረ በዳ አልፈን ወዲት ልንሄድ ነው?» ብለው ጠየቁት።

መቃሪም ጣቱን ከንፈሮቹ ላይ አጋድሞ «ስዚህ ሽሹ!» አላቸውና ወደ በእቱ ገብቶ መገሪያውን ዘጋና ተቀመጠ።

17/ ይኸው አባ መቃርስ እንዲህ ብሎ ተናግሯል፡-

«ስውን የምትቆጣ ከሆነህ እንተ ራስህ በቁጣ ታገሰህ ስለምትሄድ የምታስደስተው ስሜትህን ነው! ስለዚህ ሌላውን በቁጣ አድናለሁ ብለህ ራስህን የምታጣ ሰው አትሁን!»

18/ ቅዱስ አባ መቃርስ ገና በንጥር ሳለ አንድ ሌባ በሌሊት መጥቶ የነበሩትን ጥቂት ቁሳቁሶች ሲዘርፈው ስለ ተመለከተ ወደ ሌላው እንግዳ ሰው መስሎ በመጠጋት የዘረፈውን ሁቃ ይሆት በመጣው አጋሰስ ላይ ሲጭን አብሮ ያጫጭነዋል።

ሌባው ወደ መጣበት ተመልሶ ሲሄድ መቃርስ በታላቅ የነፍስ ሰላም ውስጥ ሆኖ ተመለከተውና «ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና አንዳችም ልንወስድ አይቻለንም . . . » (1ኛ ጢሞ 6:7) ካለ በኋላ ቀጠል አድርጎ « . . . እግዚአብሔር ሰጠ፣ እግዚአብሔርም ነሣ፤የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን::» (ኢዮ 1:21::) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ተናገረ::

19/ አንድ ጊዜ አባ መቃርስን «ሰው ሊጸልይ የሚችለው እንዴት ነው?» ብለው ጠየቁት::

እርሱም «ረኽርም ገለጻ ማድረግ አያስፈልግም! ሁለት እጅን በቀጥታ ዘርግቶ 'ጌታዬ ሆይ! አንተ እንደምትፈቅድና አንተ እንደምታውቅ ምሕረትህን ስጠኝ!' ማለት በቂ ነው::

ውጊያው እየበረታ የሚሄድ ከሆነ ደግሞ «እርዳኝ ጌታዬ!» በል! እርሱ እኛ የምንፈልገውን በሚገባ ስለሚያውቅ ምሕረቱን ያሳየናል!

20/ ታላቁ አባት አባ መቃርስ በአንድ ወቅት እንዲህ በማለት ተናግሯል:-

«ምስጋና ስም እንደ ማጥፋት፣ ድህነትም እንደ ብልጽግና፣ አጠትም እንደ ማግኘት ወደ አንተ ከመጡ አትሞትም:: በእርግጥም በጽናት የሚያምንና በፍቅር የሚተጋ ባልጠሩ ስሜቶች

ውስጥ ስለማይወድቅ በርኩሳን መናፍስት ከትክክለኛው መንገድ ወጥቶ በጥፋት ጎዳና ላይ ሊነዳ አይችልም::»

21/ በአንድ ወቅት ሴቲስ ውስጥ የሚኖሩ ሁለት መነኩሳት ወንድሞች ኃጢአት ስለ ሠሩ የእስክንድርያው አባ መቃርስ ያወግዛቸዋል:: ይህን ጉዳይ ጥቂት መነኩሳት አባቶች ወደ ታላቁ የግብፅ መነኩሴ ወደ አባ መቃርስ መጥተው ይነግሩታል::

ይህን የእስክንድርያ አባት መቃርስ በጣም ይወደው ነበር:: ከዚያም «የተወገዙት መነኩሳቱ ሳይሆኑ መቃርስ ራሱ ነው!» ይላል::

በታላቁ መቃርስ መወገዙን የሰማው የእስክንድርያው መቃርስ ረግረጋማው ቦታ ውስጥ ሸሽቶ ተቀመጠ:: ታላቁ አባ መቃርስ ፈልጎ ካገኘው በኋላ ትንሞች ክፋኛ ተነካክሶ መጎዳቱን ይመለከታል::

ከዚያም:- «አንተ ሁለት መነኩሳትን አውግዘህ እዚህ በቢምቢ እየተነከስህ ሲሆን ያወገዝካቸው ወንድሞች መነኩሳት ግን ለየብቻ በመንደሩ ውስጥ እየኖሩ ነው:: እኔ አንተን ሳወግዝህ ልክ በእልፍኟ ውስጥ ለብቻዋ ያለች ኮረዳ ይመስል ሸሽተህ ወደዚህ መጣህ! ሁለቱን መነኩሳት አስጠርቼ ይህ በምን ምክንያት እንደ ሆነ ጠይቄ ተረድቼያለሁ:: እኔ ግን አሁን ምን እንደ ተፈጠረ አልነገርኋቸውም:: ስለዚህ ወንድሜ ሆይ! ራስህን መርምር! በዚህ

በረከምሽው ውግዘት ላይ የጠለቀ ማስተዋል ስለ ሌለህ የሰይጣን መሳሳሻ መሆንህን ተረዳ! ለስህተትህ ግን ንሥሓ ግባ!» አለው::

በዚህ ጊዜ በደል የፈጸመው የእስክንድርያው አባ መቃርስ «አባቴ ሆይ! ቀኖናዬን ስጠኝ!» አለው::

የዚህን አባት ትሕትና የተመለከተው ታላቁ አባ መቃርስ እርሱ ምግብ የሚበላው በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ ስለ ነበር «ሂድና በሳምንት አንድ ጊዜ እየበላህ ለሦስት ሳምንታት ጹም!» ብሎ አስናበተው::

22/ አባ መቃርስ በሴቲስ ሳለ አባ ሙሴ ወደ እርሱ መጥቶ «ከዚህስ ጸሎት ውስጥ ለመኖር ብወድም ወንድሞቼ መነኮሳት ይህን እንዳላደርግ እየረበሹኝ ነው!» በማለት ነገረው::

በዚህ ጊዜ አባ መቃርስ «ቁጡ ሰው ስለ ሆንህ ወንድምህን ከአንተ ለማራቅ አለመቻልህን አያለሁ! ስለዚህ በሰላም ለመኖር ከወደድህ በበረሃው መካከል ወደሚገኘው ወደ ጴጥራ (Petra) ሂድ! በዚያ ያለ አሳብ በሰላም መኖር ትችላለህ!» በማለት ተናግሮታል::

23/ አንድ ወጣት መነኩሴ ወደ ግብፃዊው ታላቅ አባት ወደ አባ መቃርስ ቀርቦ «አድን ዘንድ የሚረዳኝን ቃል ንገረኝ!» ብሎ ጠየቀው::

እርሱም «ወደ መካነ መቃብር ሂድና የሞቱትን ስደባቸው» አለው።

መነኩሴውም እንደ ታዘዘው ወደዚያው ሄዶ ሙታኑን መሳደቡ ሳያንሰው ጥቂት ድንጋይም ወርውሮባቸው ይመለሳል። ከዚያም ለአባ መቃርስ ያደረገውን በዝርዝር ይነግረዋል።

አባም «ምንም አልመለሱልህም?» ብሎ ይጠይቀዋል።

መነኩሴውም «በጭራሽ!» ይላል።

መቃርስም «ነገ ተመልሰህ ሄደህ አወድሳቸው!» አለው።

ወጣቱ መነኩሴም አሁንም እንደ ተነገረው በማግስቱ እዚያው ድረስ ሄዶ «አባቶች ሐዋርያት! አባቶች ቅዱሳንና አባቶች ጻድቃን . . . !» በማለት ሲያወድሳቸው ቆይቶ ተመልሶ ወደ አባ መቃርስ በመምጣት «አመስግኜያቸው መጣሁ!» አለው።

እርሱም «መልስ ሰጡህ?» በማለት ጠየቀው።

መነኩሴው አሁንም እንደ ቀድሞው «በጭራሽ!» ብሎ ይመልስለታል።

በዚህ ጊዜ «ምን ያህል እንደ ሰደብሃቸው አንተ ታውቃለህ! ይሁን እንጂ አነርሱ ምንም ዓይነት መልስ አልሰጡህም!

ስታመሰግናቸውም ልክ እንደዚሁ ምንም ዓይነት መልስ አልመለስልህም! አንተም ልትድን የምትወድ ከሆንህ ልክ እንደ ሞቱት ሰዎች ልታደርግ ይገባሃል! ልክ እንደ መታኑ ለሚሰድቡህም ሆነ ለሚያወድሱህ ምንም ዓይነት መልስ የማትሰጥ ከሆንህ ትድናለህ!» ብሎ ሊማር የመጣውን ሰው ተቀብሎ አስተምሮታል።

24/ ከዕለታት አንድ ቀን አባ መቃርስ ከጥቂት መነኮሳት ወንድሞቹ ጋር ወደ ግብፅ ሲወርድ በመንገዳቸው ላይ አንድ ልጅ ለእናቱ «እማምዬ! አንድ የሚወደኝ ባለ ጠጋ ሰው አለ፤እኔ ግን አልወደውም! በሌላ በኩል ደግሞ አንድ የሚጠላኝ ድሀ ሰው አለ፤ እኔ ግን እወደዋለሁ!» አላት።

ይህን ያደመጠው ታላቁ አባት አባ መቃርስ በልጁ ንግግር ተደነቀ።

አብረውት የነበሩት መነኮሳት ወንድሞቹም «አባታችን! እንዲህ እንድትደነቅ ያደረገህ አባባል የቱ ነው?» ብለው ጠየቁት።

አባ መቃርስም «መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ባለ ጠጋ ሆኖ ቢወደንም እኛ ግን የሚናገረንን አንሰማውም! በሌላ በኩል ጠላታችን ዲያብሎስ ድሀ ሆኖ ቢጠላንም እኛ ግን የጥፋት ሥራዎቹን እንወድለታለን!» በማለት ወንድሞቹን አስተማራቸው።

ጥቁሩ አባ ሙሴ (ሙሴ ጸሊም)

(ABBA MOSES THE NEGRO)

«ዘሪ ሥው» ወይም «ጥቁሩ» በሚሉ ቅጽል ስሞች የሚታወቀው ሙሴ ንጥሪያ (Nitria) ውስጥ በጣም የታወቀ ዘራፊ ነበር። በሕይወቱ የመጨረሻ ዘመናት ውስጥ የሚያስፈልገውን የምንኩስና ሕይወት ትምህርት ያገኘው ከአባ ኤሲዶር ነው። በመጨረሻ አባ ሙሴ ከሴቲስ በረሃ ከወጡት ታላላቅ መነኮሳት መካከል አንዱ ለመሆን በቅቷል። አባ ሙሴ በአባ መቃርስ ምክር ወደ ጴጥራ (Petra) ከሄደ በኋላ ከሌሎች ሰባት መነኮሳት ጋር በአረመኔ ወራሪዎች አማካይነት ሕይወቱ በሰማዕትነት አልፏል።

1/ በአንድ ወቅት አባ ሙሴ በዝሙት መንፈስ ስለ ተፈተነ ከፍተኛ ውጊያ ውስጥ ገብቶ ነበር። በዚህ ጊዜ በአቱ ውስጥ ለመቆየት ስላልቻለ ከዚያ ወጥቶ ወደ አባ ኤሲዶር ሄደ። አባ ኤሲዶር ግን ወደ በአቱ ተመልሶ እንዲገባ አጥብቆ አሳሰበው።

ይሁን እንጂ «አባቴ አልችልም!» በማለት አባ ሙሴ አሻፈረኝ አለ።

በዚህ ጊዜ አባ ኤሲዶር ከፍ ወዳለ አርከን ላይ ይዞት ከወጣ በኋላ «ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ተመልከት!» አለው።

አባ ሙሴ ጸሊም ብዛት ያላቸው የርኩሳን መናፍስት መንጋ በአየር ላይ እየበረሩ ጥቃት ከመሰንዘራቸው በፊት ሁካታ ሲፈጥሩ ተመለከተ::

ከዚህ በኋላ ደግሞ አባ ኤሲዶር «ወደ ምሥራቅ አቅጣጫ ተመልከት!» አለው::

በዚህ ጊዜ ከቁጥር በላይ የሆኑ ቅዱሳን መላእክት በክብር ብርሃን ደምቀው ይመለከታል::

በመጨረሻ አባ ኤሲዶር «በስተ ምሥራቅ አቅጣጫ የተመለከትሃቸው ከእግዚአብሔር ቅዱሳን ሰዎችን ይራዱ ዘንድ የተላኩ ቅዱሳን መላእክት ሲሆኑ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ የተመለከትህቸው ደግሞ ቅዱሳን ሰዎችን የሚዋጉ ርኩሳን መናፍስት ናቸው:: ከእኛ ጋር ያሉት አሁን ከምትመለከታቸው የበለጠ ታላቅ ቁጥር አላቸው::» አለው::

አባ ሙሴ ይህን ነገር ከተመለከተ በኋላ ድፍረት ስላገኘ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ በአቱ ተመልሶ ገባ::

2/ ከዕለታት አንድ ቀን በሴቲስ ያለ አንድ መነኩሴ ስሕተት ፈጸመ:: ወዲያውኑ በጉዳዩ ላይ የሚመክር አንድ የመነኮሳት ጉባኤ ተሰበሰበ:: በስብሰባው ላይ እንዲገኝ አባ ሙሴ ሲጠራ ወደ ጉባኤው አልወጣም ብሎ በበአቱ ቆየ::

እንደገና አንድ ታላቅ አባት «ሁሉም አንተን እየጠበቁህ ስለሆነ ፈጥነህ ድረስ!» በማለት መልሰው ላኩበት::

በዚህ ጊዜ ከነበረበት ተነሥቶ ወደተጠራበት የመነኮሳት ገባኤ ሄደ:: ወደዚያ ሲሄድ ግን አንድ ከበታቹ የተቀደደ ጣሳ ውስጥ ውኃ ጨምሮ ይዞ ነበር::

በዚያ የነበሩ መነኮሳት ወንድሞቹ በእጁ የያዘውን ተመልክተው «ይሄ የያዝከው ምንድር ነው?» ብለው ጠየቁት::

በዚህ ጊዜ አባ ሙሴ ጸሊም «ኃጢአቶቼ ከኋላዬ እንደዚህ እየተንጠባጠቡ ሲከተሉኝ አልታዩኝም:: ይሁን እንጂ ዛሬ በሌላ ሰው ስሕተት ላይ ለመፍረድ እዚህ ተገኝቼያለሁ!» ብሎ መለሰላቸው::

በዚያ የተሰበሰቡት አባቶች ይህን ሲሰሙ አባ ሙሴ ጸሊምን ይቅርታ ከመጠየቅ ውጪ ሌላ ቃል ሊናገሩት አልደፈሩም::

3/ በሌላ ቀን ሌላ ዓይነት ገባኤ በሴቲስ ውስጥ ሲካሄድ በዚያ ያሉት መነኮሳት አባቶች ሙሴ ጸሊምን ለመፈተን በንቀት ዐይን እየተመለከቱት «ይህ ጥቁር ሰው ለምን ወደ እኛ መጣ?» እያሉ ተናገሩ::

አባ ሙሴ ጸሊም የተናገሩትን ቢሰማም ምንም መልስ አልሰጣቸውም:: ገባኤው ከተጠናቀቀ በኋላ እነዚያ አስቀድመው

የተናገሩት አባቶች ወደ እርሱ ቀርበው «አባ! ንግግራችን እንዴት አሳሳዘነህም?» ብለው ጠየቁት::

«አሳዝኖኛል! ይሁን እንጂ ዝምታን መርጬያለሁ!» ብሎ መለሰላቸው::

4/ አባ ሙሴ ጸሊም ምንኩስናን ሲቀበል ካህናቱ ነጭ ካባ አልብሰውት ነበር::

ሊቀ ጳጳሱም «አየህ አባ ሙሴ! አሁን ሙሉ ለሙሉ ነጭ ተጎናጽፈሃል!» አለው::

አባ ሙሴ ጸሊም ግን «ብፁዕ አባቴ ሆይ! በእርግጥ እርስዎ ያሉኝ ነገር ለውጪ ገጽታዬ ትክክለኛ አገላለጽ ነው:: ውስጣዊ ገጽታዬን የሚመለከተኝ ጌታ ግን ምን ይለኝ ይሆን?» በማለት የሚሰማውን በጥያቄው ውስጥ መለሰለት::

እዚህ ላይ ሊፈትኑት የወደዱት ሊቀ ጳጳስ ካህናቱን ጠርተው «አባ ሙሴ ወደ መቅደሱ ሲገባ እየገፈተራችሁ አስወጡትና የሚለውን ለመስማት በዚያው ቆዩ!» ብለው አዘዟቸው::

ይህን ያላወቀው ሙሴ ጸሊም አገር ሰላም ብሎ ወደ መቅደስ ሲገባ «ውጣ አንተ ባሪያ!» እያሉ ከስድብ ናዳ ጋር ገፈታትረው ያስወጡታል::

መ/ሉ አሊም ከቤተ ክርስቲያን ወስጥ ካስወጡት በኋላ ራሱን «የሰውነትህ ቆዳ እንደ ጥላሸት ጥቁር ስለሆነ አንተን አስመልክተው ካህናቱ የተናገሯቸው ቃላት በእርግጥ ትክክል ናቸው፤ አንተ ሰው ስላልሆንህ ለምን ከሰው ጋር ትገናኛለህ?» በማለት ራሱን ወቀሰ።

5/ አንድ ጊዜ ሴቲስ ውስጥ ላሉት መነኮሳት «አንድ ሳምንት መ/ሉ ጹመ!» የሚል የጾም አዋጅ ተነገረ። በዚህ ጾም መካከል ጥቂት ወንድሞች ከግብፅ ወደ አባ መ/ሉ አሊም ስለ መጡ ምግብ ያበስልላቸው ጀመረ።

በዚህ ጊዜ ከበአቱ ውስጥ ጭስ ሲወጣ የተመለከቱ ወንድሞቹ መነኮሳት ወደ አበምኔቱ ሄደው «አባ መ/ሉ የተነገረውን የጾም አዋጅ በመተላለፍ በአቱ ውስጥ ምግብ እያበሰለ ነው!» ብለው ተናገሩበት።

አበምኔቱም «ጾመ አልቆ ሲመጣ እናናግረዋለን!» አለ።

ሳምንቱ ሲደርስ የአባ መ/ሉን አስደናቂ የሕይወት ተሞክሮ ስላወቁ አበምኔቱ ሁሉም በተሰበሰቡበት፡- «አባ መ/ሉ ሆይ! አንተ የጠበቅኸው የሰዎችን ትእዛዛት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ነው!» ብሎ ተናገረው።

6/ ከዕለታት አንድ ቀን አንድ መነኩሴ አባ ሙሴ ጸሊም ጋር ተገናኝቶ ምክር ለመቀበል ወደ ሴቲስ ከመጣ በኋላ ቃል እንዲናገረው ይጠይቀዋል።

አባ ሙሴ ጸሊምም «ሂድና በአትህ ውስጥ ገብተህ ተቀመጥ! እርሷ (በአትህ) ሁሉንም ነገር ትነግርሃለች!» ብሎ በሰላም አሰናበተው።

7/ አባ ሙሴ በአንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ተናግሯል፦

«ሸሽቶ በብቸኝነት የሚኖር ሰው በፀሐይ የበሰሉ የወይን ዘለላዎችን ይመስላል። በሰዎች መካከል የሚኖረው ሰው ግን ያልበሰለ ወይንን ይመስላል!»

8/ አንድ የሕግ ባለ ሙያ ስለ አባ ሙሴ ጸሊም ዝና ሰምቶ ሊያየው ሴቲስ ድረስ ሄደ። ይህን ነገር የሰሙ ለሙሴ ጸሊም ሊነግሩት ተነሥቶ የዘምባባ ተክሉች ያለብት ረግረጋማ ቦታ ውስጥ ሊደበቅ ሄደ።

እዚያ ከመድረሱ በፊት በመንገዱ ላይ ጥቂት ሰዎች ያገኙትና «ስማ መነኩሴው! የአባ ሙሴ ጸሊም በአት የትኛው ነው?» ብለው ጠየቁት።

እርሱም «ለምን ፈለጋችሁት? እርሱ እኮ ጅል ነው!» አላቸው።

የሕግ ባለሙያው ወደመጣበት ተመልሶ ከሄደ በኋላ ወ
ቤተ ክርስቲያን ገብቶ «ሰዎች ስለ አባ ሙሴ ጸሊም ዝና ሲያወ
ስለ ሰማሁ ላየው አለበት ቦታ ድረስ ሄጀ ነበር:: ይሁን እንጂ እ
የምንሄድበትን መንገድ አቋርጦ ወደ ግብፅ የሚወርድ እን
መነኩሴ አግኝተን አባ ሙሴ ጸሊም ያለበትን ቦታ እንዲያሳ
ስንጠይቀው 'ለምን ፈለጋችሁት? እርሱ እኮ ጅል ነው! ም
መለሰልን::» በማለት ለካህናቱ ነገራቸው::

ካህናቱ ስለ ተጠራጠሩ «እንዲህ ብሎ የነገረህ እንዴት ያ
ሰው ነው?» ብለው ጠየቁት::

እርሱም «የነተበ ጨርቅ የለበሰ ጥቁር ሽማግሌ ሰው ነው
ብሎ መለሰላቸው::

ካህናቱ በአግራሞት ተውጠው «አባ ሙሴ ጸሊም ማለት
እርሱ ነው! እንደዚያ ብሎ የነገራችሁም እንድታገኙት ስላልፈቀደ
ነው!» አሉት::

በዚህ ጊዜ የሕግ ባለ ሙያው በሁኔታው ልቡ ተነክቶ ሄደ::

9/ አባ ሙሴ ጸሊም በሴቲስ ሳለ «የቅዱሳን አባቶቻችንን
ትእዛዛት ከጠበቅን አረመኔዎች ወደዚህ ቦታ እንደማይመጡ ስለ
እግዚአብሔር ፊንታ በእውነት መናገር እችላለሁ:: የእግዚአብሔርን
ትእዛዛት ካልጠበቅን ግን ይህ ቦታ ይጠፋል!» ብሎ መናገር
ያዘወትር ነበር::

፲፬/ ከዕለታት አንድ ቀን መነኰሳት ወንድሞቹ ዙሪያውን አለውት እንደ ተቀመጡ በዕድሜ የገፋው አባ ሙሴ ጸሊም «ሣራ አረመኔዎች ወደ ሴቲስ ስለሚመጡ ተነሥታችሁ ሽሹ!» አላቸው።

እነርሱም «ለንተነስ አባታችን? ከእኛ ጋር ለትሸሸም እንዴ?» ብለው ጠየቁት።

በዚህ ጊዜ አባ ሙሴ ጸሊም «እኔ ይህቺን ዕለት ስብሙ ዓመታት በፊት አጠብቃት ነበር። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ 'ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ' (ማቴ 26፡52) ብሎ የተናገረው ቃል በዚህም ይፈጸማል!» አላቸው።

በዚህ ጊዜ ወንድሞቹ መነኰሳት «አናም ከለንተ ጋር እዚሁ እንሞታለን እንጂ እንሸሸም!» አሉት።

እርሱም መልሶ «ይህ የምትሉት ነገር እኔ ስማችሁ ነገር ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም! በጽናት ለመቆምም ሆነ ላለመቆም ኢየንዳንዱ ለራሱ መወሰን አለበት!» አለ።

ከዚህ አስከትሉ ከእርሱ ጋር ለቀሩት ለሶት መነኰሳት ወንድሞቹ «ተመልከቱ! አሁን አረመኔዎቹ በረድ ላይ ናቸው!» በማለት ተናገር እንደ ጨረሰ ወደ ውስጥ ገብቶ ሁለቱም ፈጇቸው።

በዚህ መካከል ከሰባቱ መነኩሳት ሌላ አንድ መነኩሴ ሸሽቶ የገመድ ክምር ውስጥ ተደብቆ ስለ ክብር በመሥዋዕትነት ላለፉት ሰባት አባቶች ሰባት የጽድቅ አክሊል ሲወርድላቸው ተመለከተ::

11/ አንድ ቀን አንድ ወጣት መነኩሴ ወደ አባ ሙሴ ጸሊም ቀርቦ «ከፊት ለፊቴ አንድ ነገር እንዳለ ቢታየኝም ልጨብጠው ግን አልቻልኩም!» ብሎ ነገረው::

አባ ሙሴም «ብመቃብር ውስጥ እንዳለ ካልተቀበርህ በስተቀር ልትጨብጠው አትችልም!» ብሎ መልሶለታል::

12/ በአንድ ወቅት አንድ መነኩሴ ወደ አባ ሙሴ ጸሊም ቀርቦ ስለ ጠየቀው ጥያቄና ስለ ሰጠው መልስ የሰማውን አባ ጴሜን እንዲህ በማለት ገልጸታል:-

መነኩሴው:- «ሰው ሳባልንጀራው የሞተ መሆን የሚችለው እንዴት ነው?» ብሎ ነው የጠየቀው::

አባ ሙሴ ጸሊም የሰጠው መልስ «ብመጀመሪያ አንድ ሰው ለሦስት ቀናት ያህል ሞቶ በመቃብር ውስጥ እንዳለ አድርጎ የሚል ነበር::

አባ ሰራጵዮን

(ABBA SERAPION)

1/ ከዕለታት አንድ ቀን አባ ሰራጵዮን በግብዣውያን መንደር ሊያልፍ በቤቷ ውስጥ የተቀመጠች ሴተኛ አዳሪ ተመለከተና «ዛሬ ማታ ከአንቺ ጋር ሌሊቱን ለማሳለፍ ስለምመጣ ጠብቂኝ!» ብሏት ሄደ::

ሴቲቱ «ጠጣም ጥሩ!» ብላ ራስዋንም ሆነ መኝታዋን ፈጥና አዘጋጀች::

መሸትሸት ሲል አባ ሰራጵዮን ተመልሶ መጣና ወደ ቤቷ ከገባ በኋላ «መኝታውን አዘጋጀሽ?» አላት::

እርስዋም «አዎን አባ!» ብላ መለሰችለት::

በዚህ ጊዜ አባ ሰራጵዮን የቤቱን በር ከዘጋ በኋላ ወደ እርስዋ ዘወር ብሎ «በመጀመሪያ የጸሎት ሕግ ስላለን እርሱን እስካደርስ ድረስ ጥቂት ጠብቂኝ!» አላትና ጸሎቱን ይጸልይ ጀመር::

በጸሎቱ መካከል የመዝሙራት የጸሎት መጽሐፉን ገለጥ እያደረገ ካነበበ በኋላ የሴተኛ አዳሪዋን ሕይወት እግዚአብሔር ለውጦ እንዲያድናት አጥብቆ ስለ ጸለየላት ጸሎቱን ጌታ ሰማው!

በዚህ ጊዜ ሴቲቱ ከአባ ሰራጵዮን አጠገብ እየጸለየችና ኣየተንቀጠቀጠች ቆመች። የጀመረውን ጸሎት አድርሶ ሲጨርስ ኔትዮዋ ተዘርግታ ወደቀች። ከዚህ በኋላ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከጻፋቸው መልእክታት መካከል አንዱን ክፍል በስፋት አነበበና ሙሉ ጸሎቱን አጠናቀቀ።

ሴቲቱ አባ ሰራጵዮን በምሽት ወደ እርስዋ የመጣው ከእርስዋ ጋር ኃጢአት ሊፈጽም ሳይሆን ነፍሷን ሊያድንላት መሆኑን ስታውቅ ከፍተኛ ፀፀት ስለ ተሰማት እግሩ ላይ ወድቃ «አባ! አንድ የቸርነት ሥራ እንድትፈጽምልኝ እፈልጋለሁ . . . ከዚህ ቦታ አውጥተህ እግዚአብሔርን ደስ ወደማሰኝበት ቦታ ውሰደኝ!» አለችው።

በዚህ ጊዜ አባ ሰራጵዮን ወደ ደናግል ገዳም ወስዶ ለእመምኔቷ በአደራ አስረከባትና «እንደ ሌሎቹ በዚህ ገዳም ውስጥ እንደሚኖሩ እኅቶች በዚህች ሴት ላይ የትእዛዝ ቀንበር አታብዢባት! የምትፈልገውን ነገር አቅርቢላት! በገዳሙ ውስጥም እንደምትፈልግ ትዘዋወር!» አላት።

ከጥቂት ቀናት በኋላ ሴተኛ አዳሪ የነበረችው ሴት «እኔ ኃጢአተኛ ሴት ስለ ሆንሁ ካሁን በኋላ ምግብ እንዲቀርብልኝ የምፈልገው በሁለት ቀን አንድ ጊዜ ብቻ ነው!» ብላ ተናገረች።

እንደገና ከጥቂት ቀናት በኋላ «ብዙ ኃጢአት የፈጸምሁ ሴት ስለ ሆንሁ ምክብ እንዲሰጠኝ የምፈልገው በአራት ቀናት ለንድ ጊዜ ብቻ ነው!» ብላ ለአመምኔቷ አስታወቀች።

ይህን ካደረገች ከጥቂት ቀናት በኋላ አመምኔቷን «እግዚአብሔርን ሲበዛ አሳዝኜዋለሁና በሉቃን መሉ ለመሉ ዘግቼ ጥቂት ጸሎና የእጅ ሥራ እየሠራሁ እንድኖር ግንኙነቶችን በመስኮት በኩል ይሁን!» በማለት አጥብቃ ለመነቻት።

አመምኔቷ የጠየቀችውን ሁሉ ስላደረገችላት በቀሪው የሕይወቷ ዘመን እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘት ኖረች።

2/ ከዕለታት ለንድ ቀን ለንድ መነከሴ አባ ሰራጵዮንን «ለንድ ቃል ንገረኝ?» ብሎ ጠየቀው።

እርሱም መነኩሴው በበለቱ ውስጥ የደረደራቸውን ብዛት ያላቸው መጻሕፍት ስለ ተመለከተ «ለኔ ምን ልነግርህ እችላለሁ? የመበለቶችንና የእንለሙታንን ሕይወት ተቀብለህ በመጽሐፍ መደርደሪያህ ላይ ደርድረኽዋል!» ብሎ መለሰለት።

3/ አባ ሰራጵዮን በለንድ ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር። «የንጉሡ የነብር ዘቦች በፊት ለፊቱ በተጠንቀቅ ሲቆሙ ወደ ግራም ሆነ ወደ ቀኝ አይመለከቱም። ልክ እንደዚሁ ለንድ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ሲቆም ሁል ጊዜ በፍርሃት ውስጥ ሆኖ

እርሱን ሊመለከት ይገባዋል። ይህን የሚያደርግ ከሆነ ጠላቱ የሚያመጣበትን ጥቃት ፈጽሞ አይፈራም።»

4/ በአንድ ወቅት አንድ መነኩሴ ከአባ ሰራጵዮን ጋር ለመገናኘት ወደ እርሱ ይሄዳል። ለነገሩ መነኩሴው የጠራው አባ ሰራጵዮን ሲሆን ይህንንም ያደረገው አዘውትሮ እንደሚያደርገው ጸሎት እንዲጸልይለት ነው።

ይሁን እንጂ በአባ ሰራጵዮን የተጠራው መነኩሴ እንደ ገዳሙ ሥርዓት ከሆነ እኔ ይህን ልፈጽም የማይገባኝ ኃጢአተኛ ሰው ነኝ በማለት ላለመሄድ ይወስናል። በመቀጠልም አባ ሰራጵዮን የሰውየውን እግር ያጥብ ዘንድ ቢጠራውም የቀደመ ምክንያቱን በድጋሚ በማቅረብ ፈቃደኛ አለመሆኑን ይገልጻል። በዚህ ጊዜ አባ ሰራጵዮን መነኩሴው ሰው ከእርሱ ጋር ምግብ እንዲበላ ይጋብዘውና አብረው ይበላሉ።

በመጨረሻ አባ ሰራጵዮን ለመነኩሴው በተግሣጽ ቃል፦ «ልጄ ሆይ! መንፈሳዊ ዕድገት ለማምጣት የምትፈልግ ከሆነህ ለራስህና ለምትሠራው እጅ ሥራ ትኩረት ስጥ! በበለትህ ውስጥ ከመቆየት ይልቅ ከበለትህ ወጥተህ መቆየት ለለንተ ምንም የሚጠቅም ነገር አያስገኝልህም!» አለው።

በዚህ ጊዜ እንግዳ ሆኖ ለመጣው መነኩሴ እነዚህ ቃላት ጥፋቱን ስለ ገለጠበት ፊቱ በድንጋጤ ተለዋወጠ!

ይህን የተመለከተው አባ ሰራጵዮን ቀጠል አድርጎ «እስካሁን ድረስ ራስህን ምንም የማትጠቅም ኃጢአተኛ እያደረግህ ስትወቅስ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ እኔ በፍቅር ውስጥ ሆኜ ስገሥጽህ ግን ሙሉ ለሙሉ ተበላጨህ ስለዚህ ትሑት ሰው ለመሆን ከፈለግህ ሌሎች እንት ልትቀበል የማትፈልገውን ነገር እንድትቀበል ግድ ሲሉህ «እሺ» ብለህ ለመታዘዝ ትጋ ከዚህ በተጨማሪ በልብህ ወደብ ላይ ብዙ ታላትን እታስጠልልክ» አለና መከረው፡፡

ከዚህ በኋላ ይህን የሽማግሌውን የአባ ሰራጵዮንን ምክር የሰማው መነኩሴ ይቅርታ ጠይቆት በንቃት ወደ በአቱ ተመሰሰ፡፡

በቅውን ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን!!



Selections From

THE SAYINGS

Of

THE DESERT FATHERS

With Kind Permission

Of

Cistercian Publishing

Title of the book:- The Sayings of the Desert Fathers.

Name of the Translator:- Sister Benedicta Ward

Publisher:- Cistercian Publishing

Address of the published:- WMU Station, Kalamazoo,

Michigan 19008/USA

Copyright, 1975

ከዚህ ቀደም በተርጓሚው ተተርጉመውና ተዘጋጅተው ለአንባቢያን የቀረቡ መንፈሳዊ መጻሕፍት፡፡

1. የተራራው ስብከት
2. የዲያብሎስ ውጊያዎች
3. የነፍስ አርነት
4. ሀብታምና ድሀ
5. የተስፋ ሕይወት
6. መንፈሳዊው ሰው
7. መንፈሳዊ ውጊያዎች
8. መንፈሳዊው መንገድ
9. የባሕታውያን አባቶች ሕይወት
10. መንፈሳዊ ጸም
11. እግዚአብሔርና ሰው
12. መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው (ክፍል 1)
13. ሲና (1ኛ መጽሐፍ)
14/ ቅድስት ድንግል ማርያም
15/ ቅንማኤ
16/ የሕይወት ልምድ
17/ ቅዱስ ቅንዓት
18/ መንፈሳዊ አገልግሎትና መንፈሳዊ አገልጋይ
19/ መንፈስ ቅዱስና በእኛ ውስጥ ያለ ሥራው
20/ መንፈሳዊ ቃላትና ጥቅማቸው (ክፍል 2)
21/ ዳግም ምጽአት
22/ አጫጭር መንፈሳውያን ታሪኮች (1-100)
23/ የክርስቲያን ቤተሰብ
24/ የእግዚአብሔር ፍቅር
25/ ጸሎት፣ ንስሓና ተመስጦ

ከመጽሐፉ የተወሰደ

"ዓሣ ከውኃ ውስጥ ከወጣ በኋላ ለረዥም ጊዜ ከቆየ እንደሚሞት ሁሉ ከበአታቸው ወጥተው የሚንቀዋለሉና ውድ ጊዜያቸውን ከዓለማውያን ሰዎች ጋር የሚያሳልፉ መነኮሳትም የውስጥ ሰላማቸውን ኃይል ያጡታል፡፡ ስለዚህ ዓሣ ወደ ባሕር ለመግባት እንደሚጣደፍ እኛም ወደ በአታችን ልንጣደፍ ይገባናል፡፡ ይህን የምናደርገውም በውጪ ከቆየን ውስጣዊ ንቃታችንን እንዳናጣው በመፍራት ነው።"

አባ እንጦስ

◆◆◆

"ራስን መውቀስ የመሰለውን ቀላል ሸክም ከላያችን ላይ አውርደን ከጣልን በኋላ አሁን የተሸከምነው ራስን ማጽደቅ የተባለውን ከባድ ሸክም ነው!"

አባ ዮሐንስ ሐጼር፡፡

◆◆◆

"ሥጋ የሚበረታው ነፍስ በደከመችበት መስፈሪያ መጠን ሲሆን ነፍስም የምትበረታው ሥጋ በደከመበት መስፈሪያ መጠን ነው፡፡"

አባ ዳንኤል፡፡

◆◆◆

"ምስጋና ስም እንደ ማጥፋት፣ ድህነትም እንድ ብልጽግና፣ አጦትም እንደ ማግኘት ወደ አንተ ከመጡ አትሞትም፡፡ በእርግጥም በጽናት የሚያምንና በፍቅር የሚተጋ ባልጠሩ ስሜቶች ውስጥ ስለማይወድቅ በርኩሳን መናፍስት ከትክክለኛው መንገድ ወጥቶ በጥፋት ጎዳና ላይ ሊሄድ አይችልም፡፡"

ታላቁ አባ መቃርስ፡፡

◆◆◆

"ጌታዬ ሆይ! በፊትህ ምንም ዓይነት መልካም ሥራ ባልሠራም እንደ ቸርነትህ አቁመኸኛል! ስለዚህ ከአሁን በኋላ መልካም መሥራትን ስለምጀምር እባክህ አትተወኝ!"

አባ አርሳኔዎስ፡፡

ኅትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ.የተ.የግ.ማኅበር
011 156 53 52

ዋጋው ብር 35.00